# በወርሃ ሚያዝያ በስደት ለተሰዉት ወገኖቻችን መታሰቢያ ይሁን

ብ
ቀ
ላ

## ብቀላ

ብቀላ ብጠቁር፤ ብረዝም ባጥርምም
ስደት ቤቴ ሆኖ፤ ደፋ ቀና ብልም
ባህዳን አረቦች፤ ቢሳለቁብኝም
ቡችላቸው ወያኔም፤ በዘር ቢከፍለኝም
ኢትዮጵያዊነቴን በጭራሽ አልከድም።

ወያኔ ባንዳዎች፤ ቅጥረኞች ተባብረው
አገሬን ለባሕድ፤ አሳልፈው ሰጥተው
ከሃዲ ሆዳሞች፤ ለባዕዳን አድረው
ውዲቱን አገሬን፤ ለመክፈል ቢጥሩም
ኢትዮጵያ አገሬ አትከፋፈልም።





ብ
ቀ
ላ

## ብቀላ

ባገሬ ምድር ላይ፤ ሰላም ካልበቀለ
ዘረኝነት ነግሦ፤ ማቀብ ካልተጣለ
ለምን አላቀላ፤ ፍትህ እስከሌለ።

ያገራችን ድንበር፤ እስካልተከበረ
ሰንደቅ ዓላማችን፤ መደፈር ካልቀረ
ወገን በእኩልነት፤ በፍትህ ካልኖረ
ሐይማኖታችንም፤ መበረዝ ካልቀረ
ብቀላም ባቀላም አገር ለደፈረ።



ብ
ቀ
ላ

## *ብቀላ*

ኩነኔም አይደለም፤ ሐራምም አይሆንም
እግዜር አይቀይም፤ አላህ አይቆጣም
ይምስክሩ አባቶች፤ እንዲሁም ሼሆችም
በሁላችን እምነት፤ለይቅርታ አይረፍድም።



ብ
ቀ
ላ

አስተምረውናል፤ ገብተናል ቃልኪዳን
በዳይ እንዲናዘዝ፤ የገደለም ቢሆን
ወገኑን የከዳ፤ የሸጠ አገሩን
ይቅርታን ጠይቆ፤ በይፋ ወገኑን
ብቀላ እንዲጠፋ፤ ፍቅር እንዲሰፍን
እናት ኢትዮጵያ፤ ስለምትበልጥብን።
ልጆችሽ አንድ ሁነው እንዲያበለጽጉሽ።





ከጎላምንጭ April 2016